# <u>የመጨረሻው ሰይጣን</u>
# <u>ወፌ ኢላላ</u>

<u>ከበልጅግ አሊ</u>

- እንደምን ሰነበቱ እናቴ ደህና ከረሙ። ትንሽ ቀን ለስራ ወደ ውጭ ሂጄ ሳልጠይቆ ሰነበትኩ።
- መች ይመቻል ብለህ። ለኔማ ስራ ሰጥተኸን ስለዚህ ጨካኝ ሳነብ ከረምኩ።መቼስ ጉድ ነው። ቀስ እያለ ነው ወደ ጭከናው የገባው። አሁንስ ሳነበው ልቤን ባር ባር አለው። ይጨንቀኝ ጀመር።የመጨረሻው ምን እንደሚሆን ናፈቀኝ።ደግሞ ጨነቀኝ አቁሚው አቁሚው አለኝ። ምን ላደረግው ብለህ። ለሞተበት ልጁን ላጣ ማንበቡ ሲስደስት ደግሞ ደመ ክልብ የሆነው የልጆቸቸን ደም እንዴት መሰለህ የሚቆጨን።
- አይ እማማ አሁንማ ግዜው ተለውጦ የነፍሰገዳዮችን ስም አታንሱ የሚሉ በየቦታው ሞልተው። ይቀየማሉ ከዚህ መንግስት ጋር የሚደረገውን ትግል ያከሽፉብናል የሚሉ ተነስተውብን። ውሉ ሁሉ ጠፍቶ እማማ።
- አይ ልጄ ያልተነካ ግልግል ያውቃል እንዲሉ እኮ ነው።
- ችግሩን ሳያውቁት ቀርተው ብለው?
- ካለወቁትማ እንግዲያ ምን እንዲህ ያስብላቸዋል ብለህ። በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት።
- አይ ለኔማ እንግዴ ልጅነት ነው ። አለመርባት ። ወደ ትውከት መመለስ ሌላ ልለውም አልችል።መዘባነን፣ ዘመናዊነት ታሪክን ማበላሸት ነው እንጂ።
- እውነትንህን ነው ይቅር ማለት ጥሩ ነው መርሳት ደግሞ አይገባም። ለህዝብ የተሰውት ሊዘከሩ ይገባል። የገዳዮቻቸውም ታሪክ ሊነሳ ይገባል። ሁለቱም መቅረት የለበትም።
- እሱስ ልክኖት። ሊያርፉ መጥተው አሸጨነቅኮት። ስለዚህ ጨካኝ እየጨቀጨቅሁ።
- አደለም ምን በወጣህ ፈልጌ አደለም ላነበው የጠየቅሁት። ደግሞም ማወቅ አለብን ስለሞቱት ልጆቻችን ብቻ ሳይሆን ሰለ ገዳዮቹም ሊፃፍ ይገባል። ታሪክ ይህንን የጨካኞች ዘመን ሊረሳው አይገባም።አረመኔዎቹ የሰሩት ግፍ ተፅፎ ለተተኪው ትውልድ ሊቀመጥ ይገባል። አልያ ወጣቱ ትውልድ ምንም ቢሆን ሊማር አይቻልም። ለሃገራቸው ከተሰውት ጋር አገራቸውን ያቆሰሉትም ቢሆን ታሪካቸው መፃፍ አለበት።
- እውነቶትን ነው እማማ ስንቱ ነገር ተደብቆ ሚስጥር ሆኖ ይቀራል። እራሳቸው ይህንን ግፍ የፈፀሙት ተፀፅተው ሊፅፉት በተገባ ነበር። ግን አሁን እንደምናየው እንኳን በተገላቢጠሽ ሙታኑን ሊወቅሱ ነው የሚጥሩት።
- ደህና ነው ታሪክን መቼስ እንደፈለጉ መፃፍ ይቻላል ግን እውነትን መቀየር ከባድ ነው።እውነትና ንጋት እይደር ነው ይባል የለም። ለመሆኑ የአንተንስ መቼ ነው የምትነግረን?
- ላጫውቶት እንዴ ይፈልጋሉ።
- እሱኛው ይሻለኛል። ለጊዜው በዚህ በጨካኝ ሰው ጉዞ ታረክ ተጨነቀውን ልቤን በሱ ብክሰው ይሻላኛል።
- በሉ እንግዲህ አዳምጡኝ።

- እማማ ቀኑ ቅዳሜ ነበር። በደርግ ፋሽስቶችና ባንዳዎች አዲስ አበባ ተጨንቃለች። የኢሕአፓ አባላትም ሆነ ደጋፊዎች በተገኙበት ይታሰራሉ፣ ይገረፋሉ፣ ይገደላሉ።ሰደት፣እስር፣ሀዘን፣ሁሉንም ቦታ ውጦታል። የመከራ ዘመን ስለነበር እያንዳንዳችን ወጥተን እስክንመለስ ስለማናምን እንደሚያስታውሱት ከቤት ተሰነባብተን ነበር የምንወጣው። ቀይ ሽብር መቼ እንደተጀመረ ባይታወቅም የዛሬው ቅዳሜ ግን መከራና ስቃይ ያንዣበበት ቀን ነበር። አካባቢው ሁሉ ያሰፈራል። ባንዳና አንጃ ተባብው ለነፃ እርምጃ ወጥተዋል። ነፃ እርምጃ ተጧጡፏል።አሰሳም በየቤቱ እየተከላኼደ ነው ።በአሰሳ ስም ዘረፋም ቀጥሎአል።ሬዲዩኑና ቴለቪዥኑ የሚያወራው ገደላንና እስርን ነው። መፈክሩ በየቦታ ዴሞን በዴሞፍተር ነበር።

- *ነበር እንጂ ነበር። ያን ዘመን ማን ይረሳዋል። ልጆቻቸችንን ከቤት ወጥታችው እስክትመለሱ በልባችቸን እየፀለይን ነበር የምንጠብቃችሁ ። ለጋ ሰውነታችሁን ስንመለከት በእነዚያ ፋሽሽቶች ይቀጫል እያልን ሰውነታችቸን እላችን ላይ ይንዘፈዘፍ ነበር። ልጄ ለእናት እኮ ከባድ ነው ልጇ ከመሃፀኑዋ የወጣውን ሞቱን እየጠበቀች ማሰብ። ምን ይደረግ ብለህ ሁሉንም ችለን ለእዚህ ደረስን።*

- *እማማ በጠዋት ተነስቼ ቀኑ ምን እንደሚጠብቀኝ ባለውቅም ወደ ውጭ ወጣሁ። በእያንዳንዱ ሰው ላይ የሚነበበው የጭንቀት ፊት ሁል ግዜ አይረሳኝም። በዛ ቀን አንድ ቀጠሮ አንድ በኃላ በቀይ ሽብር ከተመታ ጓደኛዬ ጋር ስለነበረኝ ከቀበሌያችን ከሚገኝ አንድ ሻይ ቤት ለመገናኘት ሄድኩኝ።  እሱ ገና አልመጣም ነበርና እሱን ለመጠበቅ ሻይ አዝዤ እሱን ስጠብቅ ወደ ውጭ ስመለከት ብዙ አብዮት ጥበቃዎች በአካባቢው ሲዘዋወሩ ተመለከትኩ። ሁለት አብዮት ጥበቃዎች ወደ ሻይ ቤቱ ገቡ። ሻይ ሊጠጡ እንጂ እኔን ፍለጋ አልመሰለኝም ነበር። በቀጥታ ወደ እኔ መጥተው ቀበሌ እንደምፈለግ ነገሩኝ። ሁኔታውን ስመለከተው አሁን ምንም ማድረግ እንደማልችል ገባኝ። ለማንኛውም ብዬ ለምንድነው የምፈለገው?ብዬ ጠየቅኃቸው። እነርሱም ጉዳዩን እንደማያውቁት ነገሩኝና አብረው እንድሄድ ጠየቁኝ። አብዮት ጥበቃዎቹ አሁንም ይታወሱኛል። አንደኛው በጣም ጥቁር ነበር ።ጥርሶቹ በሲጋራ ብዛት የበለዙ ሲሆኑ አይኑና ድዱ በጣም ቀይ ነው። በንጉሱ ግዜ ቀለም ቀቢ የነበረ ሲሆን ብዙ ግዜ ስራ አጥቶ ሲቀመጥ የቀበሌው ሊቀመንበር የቀበሌ ዘበኛ አድርጎ ቀጠረው በዛውም አብዮት ጥበቃ ሆነ። አብሮት የመጣው ደግሞ ከገጠር ስራ ግለጋ መጥቶ ሰፍር ውስጥ እህል የሚስፈጭ የነበረው ነው። ደግሞ በኃላ እደሰማሁት በጣም ጨካኝ ነበር። መቼም ሁሉንም ያውቋቸዋል።*

- *አዎ አውቃቸወቀለሁ ሁለቱንም ። አሁን በኃላ ቆይቶ ቀይ ሽብር ካለቀ ያ ቀለም ቀቢ የነበረው አብዮት ጥበቃ ገንዘብ አጎደለ ተብሎ ከቀበሌ ተባሮ እዛው እኛ ሰፈር የሚበላው አጥቶ ተቸግሮ ነበር። የሰፈሩም ሰው ደግሞ አድሞ ምንም ምግብ እንኳ ሳይመፀወተው አሁን አንተን የያዙህ ቦታ ከሚገኘው ግንብ አጥር ስር ወድቆ ሲለምን ሌሊቱን ሲጮህ ቀን እኔ ላይ የደረሰ አይድረስባችሁ እያለ ሲማፀን ቆይቶ ስውነቱ ሁሉ ቆሳስሎ እዛው እንደተኛ ህይወቱ አለፈች። በቀይ ሽብር እየመታ የጣላቸው ሰዎች የወደቁበት ላይ ግፍ ቆጣሪው አምላክ፣ ለደሃ የቆመው አምላክ ከሰው ጎዳና አውጥቶ ተበቀለው። በኃላ ወያኔ ሲጋባ ገዳዮቹ ሁሉ እሱ ነው የገደለው እያሉ ማሳበብ ጀምረው ነበር። ግን ሁሉም ምስጢር አንዱ አንዱን ሲያጋልጥ ወጣ። እስቲ አቋረጥኩህ ቀጥልልኝ።*

- *ጥሩ ነው እንጂ እማማ።ጨዋታ አደል። እኔም የማለውቀውን ብሰማ ጥሩ ነው ።  ቀበሌ ስንደርስ እዛ የነበሩትን ብጠይቅ ደግሞ ምንም እንደማያውቁና አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ እንደምፈለግ ብቻ ነገሩኝ። ነገሩ ብዙ ግራ ቢገባኝም አምስተኛ ፓሊስ ጣቢያ በመባሉ ደስ አለኝ ። ምክንያቱም ይህ ጨካኝ ጓደኛ ይረዳኛል ብዬ አሰብኩ ። ወዲያው ወደ ቀበሌው እስር ቤት እንድገባ ተነገረኝ። የዚህን ግዜ ነው የነገሩን መክረር ያወቅሁት። እዛ ጨለማ ቤት ውስጥ ቁጭ ብዬ ሊደርስብኝ የሚችለውን አስብ ጀመር። እስር ቤት ለመጀመሪያ ግዜ መግባቴ ስለሆነ ፍርሃትና ጭንቀት ቢይዘኝም አላማና የደርጅት ፍቅር ለመሰዋትነት በሚደረገው ጉዞ ላይ ጥንካሬ ሰጡኝ።*

- *አይ ልጄ እኛንም እኮ ጠንካራ የሚደርገን እሱ ነበር። የእናንተን የአላማ ጥንካሬ ስናስበው ቢሞትስ ይሙት ጀግና በዋለበት ነው ብለን እናስባለን። አሁን አለ አደል ይኸው በበሽታው እያለቀ አደል ወጧቱ።ባለፈው አንዷት ልጅ በዚሁ በሽታ ሞተችና አልቃሸዋ እንዲህ ብላ ገጠመች ።*

*የቀይ ሽብር እልቂት ትዝታችን ሳይርቅ*
*የኤርትራ ጦርነት እንባችን ሳይደርቅ*
*ከሰማይ ወረደ የኤድስ መብረቅ።*
*ረገፈ አለቀ ወጣት በየቤቱ*
*ደሞ ለዚህኛው ምን ትል ወላጅቱ።*

*አለቅሰው ቸገረኝ በዛ እና ነገሩ*
*ሰው ወዴት ይደርሳል ከገዛ ሀገሩ።*
*እገጥመው ቸገረኝ አነሳሳበት*
*ቁመናው እንዳልል በቁም ጨርሶት*
*አቤት ፀጉር አልል ቅሉን ትቶለት*
*አይናማ እንዳልላት አይኗን አጥፍቶት*

ጀግናም እንዳልላት አልጋ ላይ ጥሎአት
ለቅሶም አልጠቀመ እናድርግ ጸሎት
እርግማን አለብን እንዳይኖር ወጣት ።

እንደው ለኔ እንደው ለራሴ
እየዬ እላለሁ እስኪያዝ ምላሴ።

ብላ ገጥማ ሁላችንንም ስታስለቅስን ዋለች። እስቲ ቀጥል።

- ከዛ እማማ  ከአንድ ሰአት በኃላ ዝናብ ይዘንብ ጀመር። የቆርቆሮው ጩኸት ከውጭ እሰማው የነበረውን ድምፅ ስለከለከለኝ ብቸኝነት ተሰማኝ ። ዝናቡ እየቀጠለ ሳለ በሩ ተከፈተና ሁለት ፖሊሳች ገቡ። እጄን በእግር ብረት አስረው ይዘውኝ ወጡ። በዛች በጠባቡዋ መንገድ የሰፈሩ ሰው እየጮኸ ይዘውኝ ወደ መንገዱ ሄዱ። ከዛም ፓሊሶቹ እየተጣደፉ ይዘውኝ ወደ አስፋልቱ ወጣን። ፓሊሶቹ ምን እንደሚደርስብኝ ቢያውቁም አሁን ደርስህ ትመለሳለህ ለጥየቃ ብቻ ነው የምንፈልግህ አሉኝ። ምንም ማድረግ ሰለማልችል በቀጥታ ወደ ፊት አብሬያቸው ሄድኩ ። ማምለጥ የሚቻል አደለም እንዲያውም አይሞከርም። ወደ መኪናው ስንሄድ ያሳዩን የጥላቻ ፈገግታ ከአይኔ ላይ አይጠፋም።በዛ ሰአት ደግሞ የበለጠ ከባድ ሁኔታ እንደሚጠንቀኝ ተረዳሁ። ፈገግታውን ለመጀመሪያ ግዜ ያየሁት ቢሆንም በውስጡ ጨካኝነት እንዳለው አልተጠራጠርኩም። ይህንን ፈገግታ ብዙ ግዜ ካዛ በኃላ አይቸዋለሁ። በተለይም ቀይ ሽብር በተፋፋመበት ግዜ በገዳዮች ላይ በብዛት አይቸዋለሁ ። እብሪት የተሞላ ፈገግታ ሆኖ እኔ አደለሁም ሌሎቹ ናቸው ለማለት የሚደረግ ሙከራም ይመስላል። ከዛም ወደምትጠብቀን ቮልስ ዋገን መኪና ውስጥ ገባንና ወደ አምስተኛ ፓሊስ ጣቢያ ተጉዘን ደረስን ። ጓደኛዬን ለመፈለግ ፓሊሶችሁን ብጠይቃቸው ለስራ ወደ ውጭ አገር ሄድዋል አሉኝ ።እስቲ ከኑዛዜው ውስጥ ስለኔ የፃፈውን ላንብብሎት።

ውድ ጓደኛዬ

„ዛሬ የምተርክልህ አንተን የሚመለከተውን ነው። በንፁህ ልቦናህ አንብበው። አንተነትህን ይቀይርሃል ብዬ አላምንም ግን ብታውቀው ለኔ ኑዛዜዬ ነውና ሁሉንማ ሀጥያቴን ስለሚያጠቃልል አንብበው። አንተ እንደምትፈለግ በሰማሁ ግዜ ድንጋጤ ተሰማኝ። ይህም አንተ ሆነህብኝ ነው እንጂ ሌላ ቢሆን ደስታ እንጂ ድንጋጤ የሚባል በእኔ ላይ አያልፍም። ግን ሁኔታውን አንተም እንደምትረዳው ከሌላ ቦታ የመጣ ስለሆነ ላቆመው እንደማልችል ገብቶኛል ። አንተን ቀበሌ መጥቼ ለመውሰድ ጥረትም ፍላጎትም አላደረግሁም ። ለሚያመጡህ ፓሊሶች እኔ ወደ ውጭ ለስራ እንደሄድኩ እንዲነግሩህ ያደረግሁትም እኔ ነኝ ። በዛውም ደግሞ ፓሊስ ጣቢያው እንዳትቆይ ያደረግሁም እኔ ነኝ ። በማግስቱም ወደ ደርግ ፅህፈት ቤት እንድትወሰድ ያደረኩትም እኔ ነኝ። ለሁሉም ምክንያት አለኝ ግን ያሳምንህ አያሳምንህ አላውቅም ባያሳምንህስ ምን ልዩነት አለውና።ማድረግ የምትችለውን ሁሉ እያደረግልኝ ነው። ያ ሁሉ ወንጀሌን ሳታውቀው ቀርተህ አደለም ይህን ሁሉ እርዳታ ስታደርግልኝ የቆየኸው።አምስተኛ ፓሊስ ጣቢያ ብትቀር እኔን ታገኘኝአለህ ብዬ ነው። ደርግ ፅህፈት ቤት ደግሞ አንተ ስትገረፍ አንድ ነገር ብታምን ወይም ብትናገር እኔን እንደሰርጎገብ ያስቆጥረኛል በማለት በመፍራት ነው። ማን እንዳሳሰረህ ታውቃለህ የቀበሌችን ሊቀመንበር ለህይወቴ ያስፈራኛል በማለት አንድ ደርግ ውስጥ ለሚያውቀው ያንተንና የሌላ  ቀበሌ  ያለ ልጅ ስም ሰጥቶ ነው።“

ይህንን ነው እንግዲህ በኑዛኤው ያነበብኩት። መቼስ ምን ይደረጋል ሰው እንዲህ ሆኖ ከተፈጠረ። አምስተኛ ፓሊስ ጣቢያ ብዙ የማውቃቸው ልጆች በማግኘቴ ተረጋጋሁ። እንደተለመደው ውጭ ስላለው ሁኔታ አስረዳኃቸው። ስለ አሰሳው ስነግራቸው ሁሉም ትካዜ ተሰማቸው። ውጭ ምን እየተደረገ እንደሆን ስላወቁ ተበሳጫጩ።

አምስተኛ ፓለስ ጣቢያ በጣም ትንሽም ቢሆን በፓለቲካ እስረኞች የሞላ ነበር። በነዚያ ጠባባብ ክፍሎች ያን ያህል እስረኛ ይኖራል ብሎ ማመን አይቻልም።አምስተኛ ፓሊስ ጣቢያ ግዜያዊ ማቆያ ሲሆን ግን ለብዙ ወራታት እዚያ የተሰሩ ነበሩ። ከአምስተኛ ፓሊስ ጣቢያ ደርግ ፅህፈት ቤት ሄደው ተገርፈው የተመለሱ አሉ። በግርፋት ብዛት መንቀሳቀቀስ ስለማይችሉ በላስቲክ በተሰራ መጠለያ ውስጥ ተኝተው ይታያሉ። ከሌሎቹ እስረኞች አይገናኙም። በዛ አካባቢ የነበረው የእስረኛ ብዛት ልቤን እረበሸው። ሰው ይህን ያህል ጨካኝ ሆኖ መፈጠሩ አሳዘነኝ። ግን በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ያላገለጡ

በመሆናቸው እንደገና ለመገረፍ እየጠበቁ መሆናቸውን ነገሩኝ ። በእስር ቤት  ውስጥ እንደ ዱሮው የሻማ ተብሎ እስረኛ መደብደብ መቅረቱንና በፈቃደኝነት ግን ገንዘብ ለጋራ መጠቀሚያ መስጠት እንደሚቻል ተነገረኝ። ምግብም በጋራ በተመደበልህ መቁርስ ውስጥ እንደ ደረሰህ ሳህን በጋራ እንጂ የኔን ለኔ የሚባልበት ምክንያት እንደሌለ አስረዱኝ። በህጉ ተስማምቼ ያለኝን ገንዘብ ሰጥቼ የቤቱ አባል ሆንኩኝ። ቀን ስንጫወት አምሽተን እንዴት ይተኛል ብዬ ሳስብ  ሰአቱ ደርሶ ልንተኛ ስንል ግን ሁኔታው የተለየ ሁኖ አገኘሁት። እኔ አዲስ ስለሆንኩ እግር ስር እንደምተኛ ተነገረኝ።ሌሎቹ ግን ስክ እንደሚተኙ አስረዱኝ ። ስክ ማለት በአንድ ወገብ ባንድ አቅጣጫ መተኛት ሲሆን አንዱ የሌላውን እጅ በመንተራስ ይተኛል። እንዲህ እያለ ከአንዱ ጥግ እስከ መጨረሻው ይተኛና የመጨረሻው እግድግዳው ጋር ተገፍቶ ይሰካል እንደዚህ እየተደረገ ተሰካክቶ  ይተኛል።በሙቀት ብዛት ወይም ሳይመቸው ቀርቶ አንዱ ቢወጣ ተመልሶ ለመግባት ተሰፋ የለው እግር ስርም መተኛት ስለማይችል ቆሞ ማደር አለበት።

ምንም ሳንተኛ ታደረና በማግስቱ ጠዋት ስሜ ተጠራ። ብዙዎቹ ምን አልባት ልትፈታ ይሆናልና አትስጋ ቢሆንም በርታ አሉኝ። እኔም ተሰናብቻቼው ወጣሁ። ውጭ ግን የጠበቀኝ ሌላ ነው። ሁለት ሰዎች እጄን በእግር ብረት አስረው አጣድፈው ይዘውኝ ወደ አንድ ታክሲ ውስጥ አስገቡኝ። ጋዜጣም ሰጥተው ጮክ ብዬ እንዳነብላቸው ጠይቀውኝ ጉዞ ተጀመረ። አዲስ አባባ በወታደር ተከባለች። አሰሳ እንደተጀመረ ተረዳሁ ።ስለ ጓደኞቼ አሰብኩ። ምን እንደሚገጥመኝ አሳሰበኝ። ጉዞዬ የት እንደሆነ አሰብኩ። በአሁኑ ግዜ ስንት ወጣቶች ተገድለዋል የሚለውን ለመገመት አልቻልኩም። ስንጓዝ ቆይተን ደርግ ፅህፈት ቤት ስንደርስ ታክሲዋ ታጥፋ ወደዛ አመራች። አሁን የት እንደሚወስዱኝ ገባኝ። እነዛ አምስተኛ ፓሊስ ጣቢያ ወድቀው የነበሩ የተገረፉ ጓዶቼ ትዝ አሉኝ ። በቅርብ እንደምደባለቃቸውም አሰብኩ ።መኪናው ቆመና ውረድ ብለው በሽጉጥ ሰደፍ እየደበደቡ ወደ አንድ አነስተኛ ክፍል አስገቡኝና በሩ ተዘግቶ ሄዱ ። በክፍሏ ውስጥ በጣም ትንሽ የሆኑ እስረኞቸች አገኘሁ ። ሰላምታ ሰጥቼ ለመቀመጥ ወደ አንዱ ጥግ ሞከርኩ ። ምንም ላምነው የማልችለው ሆነብኝ ። ሰው እንዴት ሌላውን ሰው እንዲህ ሊያደርግ ይችላል ብዬ አሰብኩ። እዛ ክፍል ውስጥ የነበሩ ጓዶች ተቀጥቅጠዋል፣ስጋቸው ተተልትሏል ፣ ተልቶአል ፣ተበላሽተዋል ፣ ክፍሉ ይሸታል ። ድምፃቸው ደክሟአል ፣ ነገ ምን እንደሚገጥመኝ አወቅሁ ። ተነሳሁ ምን ልረዳቸው እንደምችል ጠየቅኋቸው።

ብዙዎቹ በጣም ስለደከሙ ምንም መናገር አልቻሉም። ግማሾቹ ፈገግታ ያሳዩኛል። ሁሉም ግን ጥንካሬያቸውና የአላማ ፅናታቸው የደረሰባቸውን ስቃይ እንዲቋቋሙት እንደረዳቸው ገመትኩ።እማማ እዛ የሰይጣን ቤት ውስጥ አግብተው ያገቱዋቸው በጥይት  የተመቱት፣ በዱላ የተቀጠቀጠቀጡት፣ በእሳት የተለበለቡት ፣ በሳንጃ የተወጉት ፣ ሁሉም ምን እንደሚጠብቃቸው ባያውቁም ሞት ግን በቅርብ እንዳለ እውቅ ነበር።

ቀኑ እየገፋ ሲሄድ የአሰሳው ውጤት ነው መሰል የእስረኛው ቁጥር እየጨመረ መጣ። ያቺ ትንሽ ክፍል ተጨናነቀች። የአንዳንዶቹ ድምፅ እየሰለለ እየራቀ መጣ። እርቀውም አደል ሙቀቱ ሲበዛ ፣ ውሃ ጥሙ ሲቃጥል፣ በግርፍ ፣በጥይት፣ የተጎዳ ሰውነት እየደከመ ስለመጣ ነው ። ስለምግብ ምንም ላወራዎት አልችልም። ምግብ የሚባል ከአሰሩን ሰዎች አልታሰበም ። በረሃብ ብናልቅ ደስታቸው ነው። አንዳንድ ጊዜ ያዘነ ወታደር የተረፈውን ትራፊ ለደከሙት ስጥዋቸው ብሎ ሲሰጥ ነው ምግብ የሚገኘው። ወይም በተሰበሰበ ገንዘብ በደርግ ፅህፈት ቤት ከሚገኝ ቡና ቤት ያለው ተገዝቶ ይመጣ ነበር። ለመቃመስ ያህል እንጂ ምንም የሚጠቅም ሆኖ አደለም። በዛ ርሃብ ውስጥ የነበረውን መተሳሰብ ሳስበው እንዴት አድርጎ እንዳጠናከረኝ መናገር አንችልም። ከስውነታችን የሚወጣ ላቦት እራሳችን ላይ መንጠባጠብ ጀመረ። አይነጋም የለምና ነጋ።

*አይነጋም የለምና ቀኑ ነጋ*
*የስቃይ ቀን ሊጀመር*
*ጣርና ሞት ሊፈራረቅ*

*አንዱ ሊሸለት*
*ሌላው ሊወቀጥ*
*ብረት በቁስሉ ገብቶ ሊጎረጎር*
*በእሳት ጀርባው ሊቀቀል*
*ጠርሙስ እብልቱ ላይ ሊንጠለጠል*
*ብልቱን ለማኮላሸት ሊወቀጥ*
*ጥፍሩ በመንጠቆ ሊመነጠቅ*
*አፉ በእራፊ ሊጎሰር*
*ጌሾ ወቀጣ በሰው ሰጋ ላይ  ሊጀመር።*

*አይነጋም የለምና ቀኑ ነጋ*

*ጡቷ በሳንጃ ሊጎጠጎጥ*
*ብልቷ በእሳት ሊቃጠል*
*ምድረ  ባንዳ በላይዋ ላይ ሊሳለቅ*
*ከመሬት ደፍቶ ጸጉሯ ሊጎትት*
*በባንዳዎች ክብሯ ሊደፈር።*

*አይነጋም የለምና ቀኑ ነጋ*

*በኤሌትሪክ ሲጋ ሊጠበስ*
*አካል  ሊበታተን ሊቆራረስ*
*ጣታ  ሊቆረጥ*
*አይን ሊጎጠጎጥ*
*በፊንጢጣ እንጨት ሊሽነጥ*
*አጥንት  ሊሰበር*
*ወገብ ሊደቅ ሊሰባበር*
*ደረት በወታደር ጫማ ሊረገጥ*
*እጅ ታስሮ ሊወጠር*
*አናት ወደ መሬት ሊዘቀዘቅ*
*ደም ወደ ጭንቅላት ሊሽቆለቆል*
*እግር ወደ ላይ ሊቀለበስ*
*ጨካኝ እሱን አየየ ሊፍለቀለቅ*
*ሊደሰት ሎቤ ሊረግጥ*
*የጨካኝ ልቡ ሊምነሰነስ*

*የእናት ማዕፀን ሊንቦጨቦጭ*
*የአባት ክብሩ ሊደፈር*
*የሃገር ክብሩ ሊገደል*
*የወጣት ተስፋው ሊጨልም*

*አይነጋም የለምና ቀኑ ነጋ*

*ጨካኝ ክፍሉን ደም በደም ሊያደርግ*
*ባንዳ ፋሽሽት ሊጨፍር*
*ጨካኝ በጭካኔው ሊደስት*
*የሰይጣን ግብር ሊገበር።*

*አዲስ አበባን በአስከሬን ሊሞላ*
*ሃዘን በየቤቱ ሊያስገባ*
*ጨካኝ ልቡ ላይሳሳ*
*እርጉዝ በሳንጃ ሊወጋ*
*ህፃን ገድሎ ሊፎክር*
*ሽማግሌ አዋርዶ ሊኩራራ*
*አሮጊት ሰድቦ ሊያስካካ*

*አይነጋ የለምና ቀኑ ነጋ*
*የስቃይ ቀን ሊጀመር*
*ጣርና ሞት ሊፈራረቅ*
*አይነጋም የለም ቀኑ ነጋ*
*አይነጋም የለም ቀኑ ነጋ።*

በመጀመሪያ ማን ይጠራ ይሆን የመጀመሪያ ጥያቄ ሆነ። ሃሳብ ሁላችንም ዋጠው። እያንዳንዳችን ስማችንን ጠላነው። ለዚህ የስይጣን ልኳንዳ ቤት ስራ ባንዶች ፣ ፋሽሽቶች ደግሞ እየተዘጋጁ ይመስላል።

የጠባቂው ቁጥር ጨምሯል። በመጀመሪያ የኔ ስም ተጠራ እንደምንም ተገፋፍቼ ወጣሁ። ቀጥሎ አንድ ሌላ ልጅ ተጠራ። አየር በማግኘቴ ትንሽ ቀለል አለኝ።

ከእስር ቤቱ ትንሽ እንደተጓዝን ወደ አንድ ቢሮ ይዘውን ገቡ። ካዛም እነርሱ ተናጋገሩና ወደ ሌላ ክፍል ወስደው መሬት ላይ አስቀመጡን። ከገራፊዎች አንዱ መጥቶ አይናችንን በጨርቅ ሸበበን ። ቀኑ ገና ከመጀመሩ ጨለመብን። ወዲያው እየገፋፉ ወደ አንድ ክፍል ወሰዱን በሩን እነደገባን በጣም የሚከረፋ ሽታ አፍንጫዬን ሞላው። እስካዛሬ ድረስ አማማ የዛ ክፍል ሽታ ከአፍንጫዬ አይጠፋም። ልክ ክፈሉ እነደገባን ነው ዱላው የተጀመረው። አንዱ እጅህን ዘርጋ ብሎ አንባረቀ። ዘረጋሁለት። ሁለቱን እጆቼን አንድ ላይ በገነድ አስሮ አፌ ውስጥ ጨርቅ ጎስጉሶ ፣ እንጨት በእጆቼ ማህል ከቶ ለሁለት ሆነው አንስተው አንድ ቦታ አንጠለጠሉኝ። ጭንቅላቴ ወደ ታች ውስጥ እግሬ ወደ ላይ ሲሆን ጌሾ ወቀጣ ይመስል ደጋግመው ውስጥ እግሬን ይገርፉኝ ጀመር። አንዱ የምትናገረው ካለ ጣትህን ቀስር ብሎኝ እነደገና ወቀጣውን ቀጠሉ ። ትንሽ ከቆዩ በኃላ እዛው ጥለውኝ ወደ ሌላው ሄዱ። ልክ እነርሱ ሲሄዱ ነው አፌ ውስጥ የተጎሰጎሰው ሻሽ የመሰለ ጨርቅ ማፈን የጀመረኝ። ወደ ጭንቅላቴ የሚመለሰው ደም ፊቴን እያሳበጠው መምጣቱ የተሰማኝ። ለጥቂት ደቂቃ የሌለውን ተገራፊ ድምፅ እየሰማሁ ተንጠለጠልኩ፦

*እማማ*

*የራስ ስቃይ ይሻላል*  
*የሰው ስቃይ ከመስማት*  
*የሰው ልጅ እንደ በሬ ሲጓጉረር*  
*ሲያጣጥር*  
*እንደሚገፈፍ በግ ወደ ታች ተንጠልጥሎ ሲቃ ሲገባ።*

ወደኔ ተመልሰው እንደገና አውራ ጣቶን በሲባጎ አስረው ወደፊት ከሚገኝ አይኔ ስለተሸፈነ ምን እንደሆነ ከማላውቀው ነገር ጋር አስሮ ቢቀበቅበኝ ስውነቴ ሁሉ መጫኛ እንዳልተደረገለት እንጨት ይንቋቋ ገባ ።

*አይ የሰው ልጅ ስቃይ*  
*በገመድ ተተብትቦ*  
*አፍ በእራፊ ተወትፎ*  
*በተንፈሻ አጥቶ መሰቃየት።*

ለኔ ያኔ ሞቼ ገሃነብ እሳት እንጂ ደርግ ፅህፈት ቤት የምድር ገሃነብ እሳት ያለሁም አልመሰለኝም።በልቤ አቡነ ዘበስማያት መድግም ስጀምር ነው ሁለተኛው ዙር የጀመረው። የአሁኑንማ ተውት እማማ እስከጭንቅላቴ ድረስ ነው ግርፉ መስማት የጀመረኝ። ስዎቹ እየተቀያየሩ ጌሾ ወቀጣውን ጀመሩ። የእጄ ስቃዬን ሳስብ መገረፌን እረሳዋለሁ ፣ መገረፌን ሳስብ የአፌን መጠቅጠቅ እረሳዋለሀ ።ቀጥቅጠው ቀጥቅጠው ቢሰለቻቸው ነው መሰል ትንሽ ጋብ አሉ ። እነርሱ ጥለውኝ ሲሄዱ ነው ሁሉም ማመም የጀመረኝ።እስቲ አሁን መሸ ሌላ ቀን እቀጥላለሁ።

አይ እማማ እነርሱ አንጠልጥለውኝ ጥለውኝ እንደጠፉ እኔም እራሼን በዚህ ታሪክ አንጠልጥዬ አልተውም። ትንሽ ቆይተው ተመልሰው እዚህ አናርኮ ላይ አናድርም ሌላ ግዜ እንደግመዋለን ብለው ከተሰቀልኩበት አውርደው በቁማጨው ቢለቁኝ እሂው እስከ ዛሬ ያለቀቀኝን የደረትና የወገብ በሽታ ተሸክሜ ቀረሁ።

እስቲ በሰላም ይክረሙ ከተንጠለጠልኩበት ከወረድኩ ሌላውን በሌላ ግዜ እቀጥላለሁ።

ይቀጥላል

በልጅግ አሊ